# የዓባይ ሴራዎች !!

**ተስፋዬ ተክሉ 03/13/14**

ኢትዮጵያ በውጭ ጉዳይ ፖሊሲዋ ከጎረቤት ሀገሮችም ሆነ ከሌሎች ሀገራት ጋር በሠላም ፣ በመከባበርና በመረዳዳት ላይ የተመረኮዘ የጋራ ተጠቃሚነት አበክራ ትከተላለች፡፡ ከየትኛውም የጉረቤት ሀገር ጋር ወደ ጦርነት ውስጥ መግባት አትፈቅድም፡፡ የትኛውም ዓይነት  አለመግባባቶች ቢፈጠሩ በውይይትና የጋራ ጥቅምን ባስከበረ ስምምነት ሊፈቱ ይችላሉ ብላ  ታምናለች፡፡ የምትከተለው መስመርና እምነት አይለወጥም፡፡

ግብጽን ምን ነካትና ያልተጠበቀና የማይታመን ጥያቄ በማንሳት የተደከመበትና ፍሬ ሲያሳይ የቆየው የሦስትዮሽ ወገን ውይይት (ግብጽ፣ ኢትዮጵያና ሱዳን) የነበረው እንዲቋረጥ ምክንያት ሆነች የሚለው ጉዳይ የአብዛኛው ዜጋ የመወያያ ርዕስ ሆኗል፡፡ ዙሪያዋን እሣት እየነደደባት ያለች መሀሏ ዳር የሆነባት፣ ሠላምና መረጋጋት ያጣች ሀገር እንዴት ይህን ውሣኔ ልትወስን በቃች የሚለው ነጥብ ኢትዮጵያ ካለችበት ወቅታዊ ሁኔታ አንጻር የተለያዩ መልሶችን ይሰጠናል፡፡ በምናልባታዊነትም ሆነ በጭብጥ የምንመለከታቸው አንኳር ጉዳዮችም አሉ፡፡

ነገረ መነሻችን የዓባይ ወንዝ ውሀ 85 ፐርሰንት ባለቤቶች አመንጪዎች እኛ ነን፡፡ መቼም ግን የዓባይን ውኃ ተጠቅመንበት አናውቅም፡፡ እኛ ስላልተጠቀምንበትም ሌሎች ሀገራትና ሕዝቦች አይጠቀሙበት ብለን አናውቅም፡፡ ይልቁንም ዓባይ ለም አፈራችንንም ጭምር እየወሰደ እኛን በድህነት ሲቀጣ ሌሎችን አክብሮና አንግሶ አኑሯል፡፡ ዓባይ ከእኛ ይዞታና መሬት በመፍለቁ የተበሳጬት ግብጾች ሳንደርስባቸው ደርሰው ፍጹም ጠላት ሁነውን ነው ቁጭ ያሉት፡፡   የእኛም ዓባይ ውኃ ብዙ ጠላት አፍርቶልናል፡፡

የመጀመሪያይቱ በምድረ በዳው አሸዋ ላይ የፀሐይ የበረሀ ሀሩር እየወረደባት የምትኖረው ግብጽ ትንፋሿ መለስ የሚለው፣ ደረቁና አሸዋማው መሬቷ የሚለመልመው፣ ነፋሻማ አየር የምታገኘው፣ ዓባይ አባ ሙላት ሲደርስላት ነው፡፡ ተሽከሞት ከሚሄደው ደለል ዝቃ ድንቅ የፍራፍሬና የአትክልት ምርት የምታመርተው፣ በውኃ ጥም የደረቀውን የህዝቧን ጉሮሮ

አንጀቱ እስኪርስ የምታጠጣው፣ ታላቅ የተባለውን የአስዋን ግድብ ገንብታ ኃይል የምታመነጨው፣ ሰው ሰራሽ ሐይቅ ሰርታ ዓሳ የምታረባውና የምታሰግረው በእኛው ዓባይ ነው፡፡ ለእኛ የተረፈን የተጠቀምበትን አንዷትም ምንም ነገር ሳይኖር ከፍጥረት እስከ ትናንት እያወደስነው፣ እየሰገድልነት፣ እየዘመርልንለት ኖርን፡፡ በሰሙም፣ በወርቁም፣ በቅኔውም በድጓውም፣ በግዕዙም፣ በማህሌቱም፣ በሰዓታቱም፣ በወረቡም፣ ጥንትም ዛሬም ዓባይ አለ፡፡ ለወደፊቱ ወደፊትም ዓባይ ይኖራል፡፡ እንግዲህ ግብጾች ከፈርኦኖችና ከተለያዩ ካሊፋይቶች ጊዜ ጀምሮ የዓባይ ውኃ መነሻ ምንጭና ፈጣሪ የሆነችውን ኢትዮጵያን በነፍጥና ጦር አልፎም ፖለቲካ ለመያዝ እጅግ ብዙ ደክመዋል፡፡ ጦር አዝምተው ከአንዴም ሁለቴ ተሸንፈዋል፡፡ ከቱርኮች ጀርባም ሆነው ሞክረዋል፡፡

በኤርትራ ጉዳይ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ትቀላቀል ወይስ አትቀላቀል ብሎ አባል ሀገራትን ሲያወያይና ሀሳብ ሲሰበስብ (በጃንሆይ ዘመን ማለት ነው) ግብጽም ከላይ ሆኜ ዓባይን እቆጣጠራለሁ በሚል ኤርትራን ማስተዳደር ያለብኝ እኔ ነኝ ብላ ተከራክራለች፡፡ በቅርቡ በወጣው የአምባሣደር ዘውዴ ረታ የኤርትራ ታሪክ መጽሀፍ ላይ በማስረጃነት ሰፍሮ ይገኛል፡፡ ይኼም ውድቅ ተደርጎበታል፡፡

ግብጽ በዚህም አላበቃችም፡፡ ኢትዮጵያ አቅም አግኝታ በዓባይ ውኃ ላይ ግድብ እንዳትሰራ በምዕራቡ ዓለምና በዐረቦች መካከል ያላትን ተደማጭነትና የፖለቲካ ሚዛን፣ ከእሥራኤል ጋር የተደረገውን የካምፕ ዴቪድ ስምምነት በመጠቀም፣ ሌሎችንም በማስፈራራት ዓለም ባንክና አይ ኤም ኤፍ፣ ዓለም አቀፍ ገንዘብ አበዳሪ ተቋማት ለኢትዮጵያ የዓባይ ግድብ ግንባታ ምንም ዓይነት ገንዘብ እንዳያበድሩ በቀጥታም በተዘዋዋሪም እርዳታ እንዳያደርጉ አድርጋለች፡፡

በዚህ ያላበቃቸው ግብጽ ከጥንት እስከ አሁን ኢትዮጵያ ሠላምና መረጋጋት ያላትና በምጣኔ ሀብት የበለፀገች ሀገር እንዳትሆን፣ አቅም ኖሯት የዓባይን ግድብ እንዳትገነባ፣ በእርስ በእርስ ጦርነትና የጎሣ ግጭት ተወጥራና ተቀስፋ እንድትኖር ለማድረግ ከትናንት እስከ ዛሬ አልተኛችም፡፡ ስታሴርና ሰትዶልት ኖራለች፡፡

የግብጽ መሪዎች በረዥም ጊዜ የስትራቴጂ እቅዳቸው ውስጥ ቀርጸው በማስቀመጥና በአራቱም የኢትዮጵያ ማዕዘናት የተነሱትን ተቃዋሚዎችና የጎረቤት መንግሥታት ሶማሌያንና ሱዳንን ጭምር ስትረዳና ኢትዮጵያን በጦርነት ውስጥ ስታምስ ኖራለች፡፡

የሶማሊያው ዚያድ ባሬ የኢትዮጵያን ግዛት 700 ኪሎ ሜትር ጥሶ ግዛቴ አዋሽ ድረስ ነው ብሎ የገባው የግብጽ መንግሥት በቢሊዮኖች አውጥቶ በገዛለትና ከዐረብ ሀገራት በእርዳታ በተገኘ ዘመናዊ ጄት ታንክ፣ መድፍ፣ የአየር መቃወሚያና የመካናይዝድ መሣሪያዎች ነው፡፡ በዚያን ወቅት ንጉሱ ከሥልጣን ከመውረዳቸው በፊት ከአሜሪካን መንግሥት የጦር መሣሪያ ከፍለው ቢገዙም ወደ ሀገር ውስጥ አልገባም ነበር፡፡

ደርግ ንጉሱ ከአሜሪካ ለኢትዮጵያ የገዙትን መሣሪያዎች እንዲሰጠውና የሶማሌያን ወረራ ለመከላከል ሲጠይቅ የጂሚ ካርተር መንግሥት በታላቅ ክህደት ከለከለ፡፡ ለኢትዮጵያ የጦር መሣሪያዎቹን አንሰጥም አለ፡፡ የኢትዮጵያን በሶማሊያ መወረር ፈቀደ፡፡ ኢትዮጵያ ግን ትናንትም አልተንበረከከችም፡፡ ወደፊትም መቼም አትንበረከክም፡፡ በጀግና ህዝብዋ እንጂ በሌላ በማንም አትተማመንም፡፡ ኢትዮጵያ ታበድሕ እደዊሀ ሀበ እግዚአብሔር እንዲሉ! ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ከፍ አድርጋ ትለምናለች፡፡ ይሰማታልም!! ታሸንፍማለች!!

ከሶማሊያ ጋር እጅግ ያልተመጣጠነ ጦርነት ገጠምን፡፡ ግን ደግሞ ያልተጠበቀና የማይታመን ታላቅ ድል አድርገን ወረራው የሶማሊያ ጦር በኢትዮጵያ መሬትና አሸዋ ሰምጦ ቀረ፡፡ ቁም ነገሩ ልብ ያለው ልብ ያድርግ ነበር፡፡ ግብጾች በሠራዊታቸው ብዛትና በነፍጣቸው እንዲሁም በአሞራዎቻቸው ብዛት ተማምነው ኢትዮጵያን ለመውረር የሚያስችል የመልክዓ ምድር አቀማመጥ የላቸውም፡፡

እንደ ትናንቱ ሁሉ በወኪሎቻቸው አማካይት የተለያዩ ሥውር የፖለቲካና የምጣኔ ሀብት ጦርነቶችን በእጅ አዙር ኢያካሂዱም ለማለት አይቻልም፡፡ ሲያካሂዱ ኖረዋል፡፡ አሁንም ያካሂዳሉ፡፡ ለዚህ ደግሞ የሀገር ውስጥና የውጭ ተቃዋሚውን በገንዘብና በማማከር በሥልጠና በመርዳት ኢትዮጵያ ያልተረጋጋች ሀገር እንድትሆን የተጀመረው የልማትና የእድገት ሥራና ግንባታ እንዲስተጓጎል አቅማቸው የፈቀደውን ሁሉ ያደርጋሉ፡፡

እያደረጉም ነው፡፡ ኦብነግን፤ ኦነግን፤ ግንቦት ሰባትን፤ ሻዕቢያን በመርዳትና በማገዝ ላይ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ በካይሮና አሌክሣንደሪያ ቢሮ እንደሰጧቸውም ይታወቃል፡፡

ግብጾች በሦስትዮሽ ድርድርና ምክክሩ እንዲሁም ውይይቱ ከመጀመሪያው ጊዜ ጀምሮ ያነሱት የነበረው መሠረታዊ ጥያቄ የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ የግብጽን የውኃ ድርሻ ይቀንሳል፤ ስለዚህም የግድቡ ግንባታ ቆሞ ወደ ድርድር ውይይትና የጋራ መግባባት ላይ መድረስ አለብን የሚል ነው፡፡

ሌላው ነጥባቸው በ1959 ግብጽና ሱዳን የዓባይን ውኃ በተመለከተ ባደረጉት የኮታ ድልድል ግብጽ 55 ነጥብ 5 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውኃ እንደምታገኝ ቀሪው የውኃ መጠን ለሱዳን ሆኖ የቀረውም በትነት ሊባክን እንደሚችል ይገመታል፡፡ ይህንን ውል ሲያደርጉ በቅኝ ገዥዎቻቸው አሳሳቢነትና ጣልቃ ገብነት የተካሄደ ነው፤ ዋናውና የዓባይ ውኃ 85 ፐርሰንት ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያ በጉዳዩ አልተሳተፈችም፡፡ የምታውቀውም ነገር የላትም፡፡ ስለዚህም ግብጾች በዓባይ ውኃ ላይ ታሪካዊ መብት አለን የሚሉት ምንም ዓይነት ታሪካዊ ሙብት  እንደሌላቸው ዓለምም አፍሪካም ያውቃል፡፡

ግብጾች (Principle of confidence building) በሚለው አካሄዳቸው ገለልተኛ የኤክስፐርቶች ቡድን እንዲቋቋም ያቀረቡትን ሀሳብ ኢትዮጵያ ውድቅ አድርጋዋለች፡፡ አስገራሚው ነገር ዓባይ  በአጠቃላይ አለው ከሚባለው 85 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውኃ ውስጥ ግብጽ የሕዝቤ ብዛት እየጨመረ ስለመጣ 81 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውኃ ይገባኛል ስትል ያቀረበችውና ሁሉንም ጠቅልዬ ልውሰድ የሚለው አቋሟ ነው፡፡

ለምን ይህን ዓይነት አቋም በዚህ ወቅት ወሰደች፤ ከጀርባዋ ምንና እነማን አሉ ለሚለው ጥያቄ መልስ ወደ ውስጥም ወደ ውጭም እንድናማትር ያስገድደናል፡፡ በአውሮፓና አሜሪካ ያሉ ጽንፈኛ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎችን ግብጽ እንደ ጥንቱ ስትራቴጂዋ ሁሉ መርዳቱን ቀጥላለች፡፡ ከፍተኛ ፋይናንስ በካይሮና አሌክሳንደርያ ጭምር ቢሮና የራዲዮ ጣቢያ ሥርጭት ፈቅዳለች፡፡ የዚህ ዋናው ግብ ጸረ ኢትዮጵያ የፕሮፖጋንዳ ቅስቀሳና ዘመቻ ማካሄድ ነው፡፡ ግንቦት ሰባት፣ ኦብነግና ኦነግ በግንባር ቀደምትነት ይገኛሉ፡፡

ሀገር ውስጥ በሠላማዊ መንገድ እንንቀሳቀሳለን የሚሉ ተቃዋሚዎችም ገንዘቡ በእጅ አዙር ይደርሳቸዋል፡፡ ይህም ሕዝቡን የመሳመንና በጥላቻ እንዲነሳ የማነሳሳት ሥራ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች በተጨማሪም የገንዘብ ድጋፍ በሚደረግላቸው የግል ጋዜጣና በተለይም መጽሔቶች አማካይነት እየተሰራበት ይገኛል፡፡

በሶማሊያ በኩል የሚንቀሳቀሰውን የጅሀድ ኃይል በሥውር መርዳትና ኢትዮጵያን ዒላማ ማድረግ አንዱ የግብጽ የቤት ሥራ ነው፡፡ እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም ሻዕቢያን ግብጽ በሁለንተናዊ መልኩ ትረዳለች፡፡ በገንዘብ በጦር መሣሪያ በሥልጠና በዚህም በኩል የግብጽ ዒላማ ኢትዮጵያ ነች፡፡

ደቡብ ሱዳን ውስጥ የተፈጠረውን የእርስ በእርስ ግጭት እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀምና ችግሩ በድርድርና በሠላም እንዳይፈታ የሚደረገውን ጥረት ከጀርባ የማሰናከል ሥራዎችም ልትሰራ ትችላለች፡፡ አንደኛውን ወገን በፋይናንስና በጦር መሣሪያ በማጠናከር በውክልና ጦርነት በኢትዮጵያ ላይ ሠላም የማደፍረስ፣ የመምታትና የመመለስ፤ የማወክ ተከታታይ ግጭትና የማበሳጨት ጦርነት እንዲፈጥር ልታሰማራው ትችላለች፡፡

በተለይ በሕዳሴው ግድብና በሌሎችም የኢትዮጵያ ግድቦች አካባቢ ግብጽ ቀጥተኛና ፊት ለፊት የሆነ ጦርነት ሳይሆን የእጅ አዙር ጦርነት ነው እየከፈተች ያለችው፡፡ ቀጣዩን የአምስት ዓመት ብሔራዊ ምርጫና የኃይል አሰላለፉን ለመቀየር ሁከትና መነሳሳት ለመፍጠር ጽንፈኛው ተቃዋሚና የግብጽ ፖለቲከኞችና ደህንነት አልመከሩም አልዶለቱም ማለት አይቻልም፡፡ አብረውም እየሰሩ ነው፡፡

በሀገርና በሕዝብ ክህደት የተሰለፉ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅምና ደህንነት አሳልፈው የሸጡ በኢትዮጵያዊነት ስም የሚንቀሳቀሱ ፖለቲከኞች የህዳሴውን ግድብ ግንባታ በምንፈጥረው ትርምስ እናስቆማለን ብለው ቃል የገቡም ይመስላል፡፡ ግብጽ በማይታመን መልኩ ዓባይ ከሚይዘው 85 ሚሊዮን ኪዮቢክ ሜትር ውኃ 81 በመቶ ይገባኛል ያለችውና የተማመነችው ከላይ የተሸረበውን ሴራ ነው ብሎ መገመት ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ ዳር አያደርሳትም ይመክናል፡፡

መሐመድ አብዱ ሙተሊብ የግብጽ መስኖ ሚኒስትር ናቸው፤ ከ1959ኙ ውልና ስምምነት በላይ 80 ቢሊዮን ኪዮቢክ ሜትር ውኃ እንፈልጋን፤ አንዲት ጠብታ ውኃ እንዲሄድ አንፈቅድም ብለዋል፡፡ የግብጹ እለታዊ ጋዜጣ ‹‹ኤ›› Masry Al Yoam” እኚህኑ የመስኖ ሚኒስትር ጠቅሶ እንደዘገበው ከኢትዮጵያ ጋር ለመደራደር ሁሉንም ቀዳዳና አጋጣሚ ተጠቅመን ሞክረናል፤ ደክሞናል፤ ተሰላችተናል ማለታቸውን ዘግቧል፡፡

ግብጽ የሕዳሴው ግድብ ግንባታ እንዲቆም በተደጋጋሚ ያቀረበችውን ጥያቄ ኢትዮጵያ ውድቅ አድርጋዋለች፡፡ የኢትዮጵያ ቴክኒካል ቲም (ቡድን) መሪ ጌድዮን አስፋው የሕዳሴውን ግድብ ግንባታ‹‹ምንም ሊያስቆመው የሚችል ነገር የለም›› ሲሉ ካርቱም ላይ ተናግረዋል፡፡ አሁንም ያለው አማራጭ ኢትዮጵያ እጆችዋን ለሠላምና ለውይይት እንደዘረጋች ሁሉ ግብጽም ወደ ሠላማዊ ውይይትና ምክክሩ መመለስ አለባት፡፡

በየዓመቱ ጥር ወር የአስዋን ግድብ በጀማል አብደል ናስር ዘመን ከዛሬ 58 ዓመት በፊት የተሰራበትን በዓል ግብጻውያን ያከብራሉ፡፡ የዘንድሮው ግን የተለየ ነው፡፡ የግብጽ ፕሬሶችና ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያው ግድቡ ሲገነባ የነበሩ ሰዎችን እያነጋገረ እያወያየ አሁን ታላቅ አደጋ ተጋርጦበታል በሚል የአርበኝነት መዝሙሮችን እያሰማ ነው፡፡

የሽግግሩ መንግሥት ፕሬዚዳንት አብደል ማንሱር የግብጽን መከላከያ ምክር ቤት አስቸኳይ ስብሰባ ጠርተው ባለፈው ወር የሕዳሴው ግድብ ሊያስከትል በሚችለው ጉዳትና ተጽዕኖ ላይ መክረዋል፡፡ በተለይ የግብጽ የግድቡ ጉዳይ የብሄራዊው ኤክስፐርቶች ቡድን አባላት በተለያዩ አጋጣሚዎች ለሚዲያው በሚሰጡት መግለጫ የሕዳሴውን ግድብ ለግብጽ ታላቅ ጥፋትና አደጋ ነው በማለት ይገልጹታል፡፡

ኢትዮጵያ የሕዳሴውን ግድብን ሥራ ስታጠናቀቅና ሲገድቡት 60 ፐርሰንት የሚሆነው የግብጽ ለም መሬት ይደርቃል፤ ይወድማል ነው የሚሉት፡፡ ግድቡ ሲጠናቀቅም በተለይ አስዋን ግድብ ለሁለት ዓመት አቅም ስለሚያጣ አይሰራም፤ ምናልባትም የህዳሴው ግድብ ቢደረመስ ግብጽን ሙሉ በሙሉ ያጠፋታል እያሉም ነው፡፡ ይህን ማራገቡን ደግሞ የግብጽ ፕሬሶች ሥራዬ ብለው ይዘውታል፡፡ ግብጾች በአዲስ መልክ ኢትዮጵያ ምንም ዓይነት እርዳታና ድጋፍ እንዳታገኝ ዘመቻ ጀምረዋል፡፡ ግንባታው የተጀመረው በራስ አቅም መሆኑንም የረሱት ይመስላሉ፡፡

ግብጾች የዓባይ ውኃ ሕይወታችንና ሕልውናችን የብሄራዊ ደህንነቶችንም ጉዳይ ነው እንደሚሉት ሁሉ የዓባይ ውኃ ለኢትዮጵያም የህልውናዋና የደህንነትዋም ጉዳይ ነው፡፡ የግብጽ የፖለቲካ መሪዎችም ሆኑ ፕሬሶች ጭብጥ ከሌለው ቅዥትና ሥጋት መውጣት አለባቸው፡፡ የሚበጃቸው እውነታውን አምኖ መቀበል ብቻ ነው፡፡

ኢትዮጵያ የዓባይ ውኃ 85 ፐርሰንት የእኔ ስለሆነ እኔ ብቻ ልጠቀም ሳይሆን ለሁላችንም ይበቃል ነው ያለችው፡፡ ስለዚህ ግብጽ ከጀርባ ማሴሩንና መዶለቷን አቁማ ወደ ሠላማዊ ውይይትና መፍትሄ መምጣት ይጠበቅበታል፡፡ ከዚህ ውጭ ያሉት መንገዶች ሁሉ ዝግ ናቸው፡፡ ቢሞከሩም ይመክናሉ፡፡ መክነዋልም፡፡